# <u>እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2017 የነበረው</u>

# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

በመደበኛ ሁኔታ በጁን ሶስተኛው አስር ቀናት የክረምት ዝናብ የምዕራብ አጋማሽ እና የመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎችን ቀስ በቀስ የሚያደርሰበት ጊዜ ነው፡፡


ባለፉት የጁን ሶስተኛው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የተሻለ ጥንካሬ የነበራቸው በመሆኑ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ያደረሰ ነበር፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች በፀሀይ ሃይል እየታገዘ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ሽፋን ምክንያት ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህል በማይጨው 33.3፣ በቻግኒ 36.7፣ በሻውራ 32.1፣ በአቦቦ 38.5፣ በቢሾፍቱ41.0፣ በበካችሴ 64.0፣ በአልጌ 33.0፣ በሊሙገነት 46.8፣ በዝዋይ 33.8፣ በኢጃጂ 39.0፣ በአድዋ 34.0፣ በአደሌ 40.5፣ በነጆ 38.7፣ በበደሌ 30.5፣ በአሶሳ 35.4፣ በቤጊ 31.2፣ በቴፒ 36.1 እና በመተማ 34.8 በሚ.ሜ. ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት ትግራይ፣ አማራ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረሪ እና ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ዞን ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ትግራይ፣ አማራ፣ ቤንሻጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ እና ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ዞን ከ5-155 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-10 ቀናት ያህል ዘንቧል (ካርታ 1 እና 2)።

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር አብዛኛው ትግራይ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር አዊ እና ምዕራብ ጎጃም፤ ቤንሻጉል ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ እና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ እና አርሲ ኦኖች እንዲሁም ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፍቾ ሸከቾ እና የቤንች ማጂ ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ።


ካርታ 1    እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2     ኢ.ኤ.ኢ ከጁን 21 እስከ 30/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3   እ.ኤ.አ  ከጁን 21 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




## እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ሶስተኛዉ የጁን አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የተሻለ ጥንካሬ የነበራቸው በመሆኑ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ በተለይም በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በአብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በአብዛኛው ኦሮሚያ፣ በድሬዳዋ፣ በሐረሪ እና በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ዞን ከከፊል ደረቅ እስከ በጣም እርጥብ መጠን ያለው እርጥበት አግኝተዋል፡፡

ይህም ሁኔታ በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አስቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት መልካም አቅርቦት እንደነበረው መገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት የሚታወቁ አካባቢዎች የነበረው በጣም እርጥበትማ የአየር ሁኔታ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛውና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተገኘው እርጥበት በስፋትም ሆነ በመጠን ዝቅተኛ ቢሆንም በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ በጎ ሚና እንደነበረው ይገመታል በተለይም በመሰብሰብ ላይ ለነበሩ የበልግ ሰብሎች (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ

# በውሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 21-30 ጁን 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በምዕራባዊ አጋማሽ ተከዜ፣ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ በላይኛውና በመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ በአባይ ምዕራባዊና ደቡባዊ ክፍል፣ በላይኛው ስምጥሸለቆ፣ ጥቂት በላይኛው አዋሽ፣ ዋቢሸበሌና እና ገናሌዳዋ አዋሳኝ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል። መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ተፋሰሶች አብዛኛው የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ የመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ የላይኛው ተከዜና አባይ ምስራቃዊ ክፍል፣ ጥቂት የመካከለኛው አዋሽ እና የታችኛው ኦሞጊቤ እንዲሁም የመካከለኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ናቸው። በተቀሩት በአብዛኛው ምስራቃዊ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸው ተሰተውሏል። የክረምቱ ዝናብ በጁን የመጨረሻው አስር ቀናት በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ  የተሻለ የእርጥበት ስርጭት እንዲኖር አስተዋፆ ያደረገ ሲሆን፤ በሰሜን ምስራቅና በምስራቃዊ የሀገሪቱ ክፍል ላይ ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል (ካርታ 5)።

ካርታ 5   እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ የመጀመሪያው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ሥፍራዎችን የሚያዳርሱበት ወይም የሚሸፍኑበት ጊዜ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ነጎድጓዳማ እና በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ይዘወተራል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት የምድር ወገብና አቋርጦ ወደ ሀገራችን እየገባ ያለው እርጥበት አዘል አየር ይበልጥ እንደሚጠናከርና ወደ ምስራቃዊ የሀገሪቱ አካባቢዎች ይበልጥ እንደሚስፋፉ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የምዕራባዊና የመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከሚፈጠር ጠንካራ ደመና ከባድ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ አዲስ አበባ፤ የአርሲና ቦሌ ዞኖች፤ የጋምቤላ ክልል፤ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ የትግራይ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የወላይታ እንዲሁም የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊከሰት እንደሚችል መረዳት ይቻላል። ከዚህም ሌላ ሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ፤ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ እና ሲቲ፣ ድሬዳዋ እና ሀረሪ፤ ከአፋር ክልል ደግሞ ዞን 3 እና ዞን 5 ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ ቦታዎች በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ።

## እ. ኤ. አ ከጁላይ 1-10/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የጁላይ የመጀመሪያዉ አስር ቀናት ሰፊ የቦታ ሽፋን ያለው የእርጥበት ስርጭት ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በትንበያው በተጠቀሱት የኦሮሚያ፤ የአማራ፤ ትግራይ፤ የጋምቤላ፤ የቤኒሻንጉልና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች በአብዛኛው መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡

ይህም ሁኔታ በተለይም የመኸር አብቃይ በሆኑና ዘር መዝራት ባልተጀመረባቸው አካባቢዎች ለዘር ምቹ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ አስቀድሞ የተሻለ እርጠበት በነበራቸውና ዘር

መዝራት በተጠናቀቀባቸው  አካባቢዎች በመብቀል ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የሚጠበቀው እርጥበት የተሻለ የውኃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ለሰብሎቹ ጤናማ እድገት መልካም ሁኔታ እንደሚፈጥር ይገመታል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ማሳ ላይ በመንሳፈፍ በቡቃያ ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊው ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም በመደበኛ ሁኔታ በእርጥበት መብዛት የሚታወቁ አካባቢዎች የማጠንፈፊያ ቦዮችንና የጎርፍ መከላከያ እርከኖችን አስቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

በአንፃሩ በመደበኛ ሁኔታቸው የእርጥበት እጥረት በሚያጠቃቸው አካባቢዎች በቂ ዝግጅት በማድረግ የሚገኘውን እርጥበት በሰብል ማሳዎች ላይ እንዲቆይ ማድረግና በተጨማሪም ከማሳ ውጪ የውኃ ማሰባሰብ ስራዎች ትኩረት እንዲያገኙ ይመከራል፡፡ በአንዳንድ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት የመጠጥ ውኃ አቅርቦትንና የልምላሜ ሁኔታውን እንደሚያሻሽል የሚጠበቅ ቢሆንም፤ የሚገኘውን ውኃ በጥንቃቄ መያዝና በተለያየ መልኩ ከሚከሰት ብክነት መከላከል ያስፈልጋል፡፡ በትንበያው ደረቅ ሆነው እንደሚቀጥሉ በተጠቆሙ አካባቢዎች አማራጭ መፍቴዎችን ከወዲሁ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

## እ. ኤ. አ ከጁላይ 1-10/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምቱ ዝናብ በብዙዎቹ ተፋሰሶች ላይ ስለሚዳረስ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖር ይጠበቃል። በመሆኑም በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ እንዲሁም በላይኛውና በመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ በላይኛው አዋሽ፣ በላይኛው ዋቢሸበሌና  ገናሌዳዋ ተፋሰሶች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተለይም የክረምቱን ዝናብ ቀደም ብለው ሲያገኙ የቆዩት ተፋሰሶች አፈሩ በቂ እርጠበት ስላለው በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ  ጎርፍ የማስከተል እድል ሊፈጠር ይችላል። በሌላ በኩል የአባይ ምስራቃዊ ክፍል፣ የመካከለኛው አዋሽ፣ ዋቢሸበሌ እና የላይኛው አፋርደናከል ተፋሰሶች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የክረምቱ ዝናብ በተጠናከረ ሁኔታ ከመግባቱ ጋር ተያይዞ የወራጅ ውሃ ፍሰት ስለሚጨምር ለምንፈልገው አገልግሎት ለማዋል ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።